## <u>ክፍል ሁለት</u>

*<u>መሳርያ የያዘው</u>*
<u>Saturday, July 17, 2010</u>

ክፍል አንዱም ይህም ጽሁፍ በውጪ አገር ያለ ወገናችንን ለመድረስ ወይ የማንበብ ፍጆታ ለመሙላት ብቻ አልተጻፈም። የታሰበበት ቦታ ለመድረስ ችግሮች እንዳሉ እያወቅንም ነው። ነገር ግን እንዳሰብነው ሀሳቡ ሀይል ከአለው መንገዱን እራሱ ይሰራል። የተፈለገው ቦታ ይደርሳል በሚል ተስፋ እንዲወጣ ፈለግን።

በክፍል አንድ ጽሁፋችን መሳርያ የያዛችሁት  በአብዛኛው ህዝብ ከተጠላው አንባገነኑ መለስ ዜናዊ ጋር ስለነበራችሁ የግንኙነት ባህሪ አንስተናል። እነመለስ ይህን ክፍል ሁሌም እንዳሻቸው የሚጠቀሙበት ሎሌያቸው አድረገው ከልባቸው እንደሚያምኑ::  ይህ አስተሳሰባቸው የተሳሳተ እንደሆነ። እንደሁሉም የተጠሉ አንባገነኖች መለስና ግብስብሶቹ እናንተ ላይ መመርኮዝ የተከለከሉ ቀን ኀይለ ስላሴ በቦልስ ሻገኗ ውስጥ ማለት እንደሆኑ ለማሳየት ሞክረናል። የአንባገነኖች ሀይል ያለው መሳርያ የያዘው ጋር ነው። አንባገነኖች መሳርያ ከያዘው ጋር ያላቸው ትስስር በፍቅርና በመተማመን ወይ በአላማ ላይ የተመሰረተ አይደለም ። በብዙ ምክንያቶች ሊበጠስ የሚችል ነው። በተሞረኮዙት ሀይል ተማምኖ መደንፋት እናንተ እስከፈቀድችሁ ብቻ የሚቀጥል ነው። ይህ በአገራችንም የተጠሉ አንባገነኖች በነበሩባቸው ሌሎች አገሮችም በተደጋጋሚ ተከስቶ የታየ እውነት መሆኑን አሳይተናል።

ለሀያ አመት መለስ ዜናዊን አይነት የተጠላ አንባገነን መወገዱን ከመፈለግ በዘለል ያልተቀናጀ ደካማ ተቃውሞ ብቻ መሳርያ ከያዛችሁት ሲዳብሰው ለምን ቆየ?።  ልጓም ሳታበጁለት የቀረ ፍላጎቱ ወይ አቅሙ ሳይኖራችሁ ቀርቶ አይደለም። ድሎት ግዴለሽ አድርጓችሁ ነው የሚለው ደሞዝተኛነት ተካብዶ በመናደድ የሚባል ነው። እነዚህ ምክንያቶች ከአልሆኑ ትክክለኛው ምክንያት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ አንስተን መልስ ለመስጠት ሞክረናል።

እስካሁን መሳርያ የያዛችሁት ያደረጋችሁት ትግል ለለውጥ ያለን ፍላጎት እንዲሰማ አድርጎ ማሳየት፤ ማጉረምረም፤ በየስብሰባው በየግምገማው የመለስ አንባገነን አስተዳደር እየሄደበት ያለው መንገድ የተሳሳተ መሆኑን በድፍረት መናገር። ተቃዋሚውን ለማፈን መጠቀሚያ መሆንን መቃወም፤ የዚህ አይነት ግዳጆች ላይ ማልገም፤ ከሰራዊቱ በብዛት መኮብለል። በመጠኑም የሽምቅ ውጊያ የሚያካሂዱ ክፍሎችን መቀላቀል ወይ ለጊዜው ለመለስ ባላንጣ ወደ ሆነችው ኤርትራ መኮብለል የመሳሰሉት ናቸው።

እነዚህ ትግሎች የመቀናጀት በሙሉ ሀይላቸው አገልግሎት ላይ የመዋል ችግር ነበረባቸው። ተራ ተደርገው የሚታዩ እርምጃዎች ግን አይደሉም። በሀይለስላሴ ጊዜ ቢሆን መንግስት መቀየር ይችሉ ይሆናል። በጊዜው የሀይለስላሴ መንግስት ላይ መሳርያ ከያዘው የነበረው ተቃውሞ ተጽኖ የማድረግ ሀይሉ ከዚህ ብዙም የተለየ አልነበረም። በደርግ ጊዜ ሆኖ ቢሆን የመንግስት ስረአቱን በደንብ ይነቀንቅ ነበር። አይደለም ፖለቲካል ጥያቄ ያላቸው አመጾች ምግብ አልጣፈጠነም ያለውን ሰራዊት ለማለዘብ ምን ያህል ጊዜ መንግስቱ በየክፍለጦሩ ይመለላስ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ምግብ አልጣፈጠኝም ብሎ ያመጸው መሳርያ በጁ ያለው ነበር። የዚህ አይነቶቹ እርምጃዎች በነመለስ ላይ ተጽኖ ለማሳደር ግን ውጤታማ አልነበሩም።

እንደውም እነዚህ እርምጃዎች መሳርያ የያዛችሁትን ከባድ ዋጋ አስከፍለዋችኋል። በአንድ ዙር እስከአስር ሺዎች ከሰራዊቱ ተባረዋል። መተዳደሪያቸውን አጥተዋል። ይህ ከጠቅላላው የሰራዊቱ ቁጥር አስር በመቶ ማለት ነው። ይህ ቁጥር ከፖሊስ ሰራዊት የተባረሩትን፤ በተጽኖ ምክንያት የከዱትን፤ የኮበለሉትን ሳይጨምር ነው። የተገደሉ በየስር ቤቱ ስቃይ የሚያዩት ቀላል ቁጥር ያላቸው የሰራዊቱ አባላት አይደሉም።

እስከአሁን የትደረጉ እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ትግሎች አላማችው ተጽኖ በማድረግ የመለስ መንግስት ወደጥሩ ይቀየራል ከሚል እምነት ነው። በአላንጣችን ኢትዮጵያዊነት የማይሰማው ነው።

የሚመራውን ህዝብ የሚጠላና ምንም አይነት ክብር የሌለው ነው። ወደጠሩም ልለወጥ ቢል አይችልም። ስልጣን ላይ ለመቆየት በውጪ አካላት አስገዳጅ ግዴታዎችን የመፈጸም ግዴታ የተጫነበት ነው። ይህ መንገድ ያልሰራው ለዚህ ነው። ይህን እውነት ለናንተ ብቻ ሳይሆን አንባገነኑን መለስ ዜናዊን ሲታገሉ  የነበሩ ብዙ ክፍሎች ሞክረውት እንደማያዋጣ በሂደት አስረግጠው ያረጋገጡት መንገድ ነው።

መሳርያ የያዛችሁት ትግሉ ላይ ድርሻ የምታደርጉ ከሆነ መለስና ግብስብሶቹን ለመልካም ማስወገድ ላይ ማተኮር አለበችሁ። ጊዜ ተወስዶ የተጠና እቅድ ያስፈልገዋል። አስተዳደሩ አናቱ ላይ መጠረብና መጣል አለበት። ይህ እቅድ የመንግስት አስተዳደሩን ሽባ የሚያደርግ፤ የግንኙነት መስመሩን የሚቆራርጥ መሆን አለበት። ውጤታማ እንዲሆን ያስፈለገውን ያህል ቁጥር ያላቸውን ዋና ዋና ሰዎች በቁጥጥር ስር ማዋልን ይፈልጋል። እነማን ናቸው? ስንት ናቸው?። አስር፤ አንድ መቶ፤ አንድ ሺ ናቸው የሚለው ቀድሞ በመረጃ ተደግፎ የሚወሰን ይሆናል። የተወሰነቱን የአመት እረፍታቸውን ሰጥቶ እቤት እንዲያርፉ  በሚኖሩበት ቀበሌ በየቀኑ ሪፖርት እንዲያደርጉ ማድረግ ይፈልግ ይሆናል። ከዋናዎቹ የስራአቱ ሰዎች እንደሚያሳዩት መገዳደር ፈጣን የሆነ ነጻ እርምጃ መውሰድም ዋና ትኩረት መሆን አለበት። እነዚህ ሰዎች ተበጥረው መታወቅ አለባቸው። ይህም ብቻ አይደለም መልሶ ሰላምና መረጋጋትን ማምጣት የሚቻልበት መንገድ በእኩል ትኩረትን የሚሻ ጉዳይ ነው።

መሳርያ በጃችሁ የሆነው ይህን ሀሳብ ተግባራዊ ለማድረግ ስታስቡ ሁለት አማራጮች እንዳሏችሁ ይታዩናል። ማንኛውንም አማራጭ ለመሞከር ሲታሰብ ከላይ ያነሳናቸው ቁምነገሮች ግን ችላ መባል በፍጹም የሌለባቸው ናቸው።የመጀመርያው አማራጭ መሳርያ በጃችሁ የሆነው እራሳችሁን ችላችሁ መለስና ግብስብሶቹን ለማስወገድ መንቀሳቀስ ነው። ይህን ማድረግ ይችላል። ተመራጭ ወይ በብዙ ምክንያቶች እኛ የምናበረታታው መንገድ አይደለም። ተመራጭ የማይሆነው ይህን ለማድረግ የሚገጥሙ መሰናክሎች መፍትሄ ሊሰራላቸው የማይችል ስለሆኑ ግን በፍጹም አይደለም። የተሻለ ውጤታማ ሊገጥሙ የሚችሉ ችግሮች መቀነስ የሚችልበት ሌላ አማራጭ ስለአለ ብቻ ነው።

ይህን እንድንል ያስቻሉን ምክንያቶቹ። ያለው ጥብቅ የሆነ ቁጥጥር። እንቅስቃሴውን የሚመራው በአመራር ላይ በአሉ በአለማረጎች መሆኑ። ከሌላው የጦሩ ክፍል ጋር እርምጃውን ለማቀናበር ተገናኝቶ ለመምከር ያለው አስቸጋሪ ሁኔታ። የአመራር ቦታውን በተዋረድ እስከታች ከአንድ ዘር የወጡ የበዙት የመለስ መንግስት እንዲቀጥል ፍላጎት ያለቸው በጥቅም በተሳሰሩ ግለሰቦች መሆናቸው። ለአለፉት ሀያ አመታት እርስ በርሳችሁ እንዳትተማመኑ በግምገማ፤ በጠራናፌ በመሳሰሉት መንገዶች የተሰራው ስራ። እነዚህን የመሳሰሉ ቴክኒካል ችግሮች ናቸው።

የመጨረሻ ግቡ መልስን ግብስብሶቹን ከስልጣን አስወግዶ አገር ከአረጋጉ በኋላ በህዝብ ለተመረጠ ስልጣኑን ለማስረከብ ቢሆንም።  ከቅርብ ጊዜ ታሪካችን ተሞክሮ በመነሳት ከበዛው ዜጋ፤ በተቃዋሚነት ተሰልፎ ከአለው ክፍል ሊኖር የሚችል ፍራቻ እርምጃውን የሚፈልገውን ድጋፍ ሊያሳጣው መቻሉ። በጦሩ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ሊፈጠር የሚችል አለመተማመን። በተመሳሳይ ከውጪ አገር መንግስታት ድርጅቶች ሊያጋጥም የሚችል ተቃውሞዎች። እነዚህ ችግሮች እንደግመዋለን ስራን፤ ማሰብን፤ ማቀድን ይፈልጋሉ እንጂ መፍትሄ ሊሰራላቸው የማይቻሉ ግን አይደሉም።

ዋናው ምክንያት ግን ይህ ትግል መልሰን ማንነታችን ለማግኘት የሚደረግ የነጻነት ትግል ነው። በማንነታችን ላይ ነው ጦርነት የተካሄደው። ይህ ጦርነት ደግሞ ከውጪያዊ አካል እስካሁንም ድረስ በደንብ የተቀናበር ድጋፍ ያለው ነው። መሳርያ የያዛችሁት ወይም አንጀቱ ያላቸው ተሰባስበው ነጻነትን ሊያመጡ ይችላሉ። እንደ ኢትዮጵያዊ የነበረንን በራስ መተማመን ኩራታችንን ግን መልሰው ሊሰጡን አይችሉም። እንደሰው ልጅነት የነበረንን ኩራት መመለስ ይመንፈልግ ከሆነ ትግሉ ቢቻል የዜጎች ሁሉ ወይ የበዛው ዜጋ አስተዋጾ ያለበት መሆን አለበት። ይህን ስናደርግና ስናሸንፍ ብቻ ነው አንገታችንን ቀና አድርገን ማንንም መመልከት የምንችለው። ኢትዮጵያዊ ኩራታችንን መመለስ የሚቻለን።

ሁለ ገብ ትግል ሲባል የሚገባን የተለያየ የትግል መንገድ ብቻ አይደለም። ዜጋው በሙሉ ትግሉ ላይ ድርሻ ይኑረው ነው። ይህ የሚሆነው ደግሞ ሁሉም ከሌላው ያልበዛ እንዳለበት ሁኔታ እንደአቅሙ የድርሻውን ሲያውቅ ነው። መሳርያ የያዛችሁት የድርሻችሁን ማወቅ አለባችሁ። ማወቅ ብቻ ሳይሆን

የድርሻችሁን መፈጸም አለባችሁ። ነገር ግን አይደለም እራሳችሁን ችላችሁ የለውጥ አካል መሆን የበዛም ድርሻ እንዲኖራችሁ የሚበረታታ የማይሆነው።

ሁለተኛውና የተሻለ ተማራጭ ሆኖ ያገኘነው መንገድ እርምጃውን እነመለስ ለመልካም መወገድ አለባቸው ብለው አቋም ከአደረጉ ጋር ትግላችሁን ማቀናጀት ነው። ይህን ስንል በተቃዋሚ ወገን ሆኖ ይህን እርምጃ የሚቃወም ይኖራል ለማለት አይደለም። ያሉበት ሁኔታ በግልጽ ለዚህ አላማ እንሰራለን ለማለት  እንደማይፈቅድላቸው የታወቀ ስለሆነ ነው። አላማው ይህን ስረአት ሊደረመስ በሚችልበት ሁኔታ ከአናቱ መጥረብ ነው። ይህ እረምጃ በዜጋው እንቢተኝነት የሚታጀብ ስለሆነ ይህ ክፍልም የራሱ ከባድ ድርሻ ይኖረዋል። ህግና ስረአትን ለመመለስ ህዝብን በማረጋጋቱ ትልቅ አስተዋጾ ማድረግ ይችላሉ።

በርግጥ መሳርያ የያዛችሁት ከተቃዋሚው ጋር የተቀናጀ እርምጃ ሲታደርጉ እርምጃው ስኬታማ የመሆኑ ወይ ያለመሆኑ ሁኔታ ከናንተ በበዛ በተቃዋሚው ብቃት  የሚወሰን ነው የሚሆነው። ስራውን በወረቀት በአለ እቅድ። በሀላፊነትና በጥንቃቄ መከወን፤ ጠንካራ የመረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም፤ ጠቅላላ ድርጅታዊ ጥንካሬን ይፈልጋል። ስራው ውጤታማ እንዲሆን በተቃዋሚ ወገን የተሰለፈውን ማሰባሰብና ሊሰማ የሚችል በቀላሉ የዜጋውን ሁሉ አመኔታ ሊያገኝ የሚችል ትብብር መፍጠር ግድ ይላል። ተቃዋሚው የህዝብን አመኔታ መስራት ሲችል የናንተንም አመኔታ በቀላሉ ያገኛል። ይህም ብቻ አይደለም ትብብሩ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ ያልቻሉትን ክፍሎች ድጋፍ እንዲኖረም ሚስጥራዊ ስምምነቶች የመቋጨቱ የስራ ድርሻም የተቃዋሚው ይሆናል።

እርምጃውን ከተቃዋሚው ትግል ጋር ማቀናጀቱ የበዙትን ስራዎች ለመስራት የተሻለ ነጻነት ወዳለው ያስተላለፋል። መሳርያ ለያዛችሁት የስራ ጫና ከመቀነሱ በላይ ሊያጋጥም የሚችል አደጋ መሰናክሎችን ይቀንሳል። በእንደዚህ አይነት እርምጃዎች የበዛው ችግር ወይ አደጋ ሊያጋጥም የሚችለው ግዳጁ ከሚፈጸምበት የመጨራሻ ሰአታት ይልቅ ቅድመ ስራዎች በሚሰሩበት ጊዜ ነው። ይህንን ችግር ይቀርፋል።

የናንተ ድርሻ መጨረሻ ላይ የሚመጣ ነው ስንል ኢላማው  ቀደም ብሎ የታወቀ በጣም ውስን ግዳጅ ነው የምትፈጽሙት ማለታችን ነው። ይህ በደንብ ለሰለጠነ በአግባቡ ለታጠቀ ከፍተኛ ቁጥር ላለው ሰራዊታችን በጣም ቀላል ስራ ነው። ነጮቹ ቁራጭ ኬክ የሚሉት አይነት ነው። ትልቁ ግዳጅ የሚሆነው ሰላምና መረጋጋትን ማስፈኑ ነው። ህግና ስረአትን ቶሎ መመለስ መቻሉ ነው።

የናንተን ድርሻ መጨረሻ ላይ የሚመጣ በማድረግ ሊኖር የሚችል የአለመተማመን ችግር ማስቀረት ይቻላል። ሊኖር የሚችል ጉዳትን በማሳነስ የናንተን ትግሉ ላይ ተሳታፊነትን እውን ለማድረግ መሞከር ብልህ መንገድ ነው። ዋናው የዚህ ጽሁፍ አላማም በተጠና የብልህ እርምጃ ያለብዙ መሰዋትነት የመለስን መንግስት  ማክተም ከሚቻልባቸው ብዙ መንገዶች ይህም አንዱ እንደሆነ ለማሳየት ነው።

በጋራ በተቀናጀ መልክ ስለሚደርግ ትግል ስንል ተቃዋሚው በአንክሮ ሊመረምረው የሚገባ ሁለት መንገዶች አሉ። የመጀመርያው መንገድ ትግሉን ከናንተ ጋር ለማቀናጀት ሲያስብ ምንም አይነት ወሳኝ ስራ ወይ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት አስተማማኝ ድርጅታዊ ስራ መሰራቱን እርግጠኛ መሆን ነው። እስካሁን በተቃዋሚው በኩል ትኩረት የተሰጠው እየተሞከረም ያለው መንገድ ይህ ነው። ይህ የተሻለ ውጤታማ ነው። ነገር ግን ሂደቱ ቀሳሳ አደጋም ያለው መንገድ ነው።

ሁለተኛው መንገድ መሳርያ የያዛችሁትን በጋራ ለትግል ማዘጋጀት ነው። ይህ ከቅስቀሳ ስራ በፍጹም የተለየ ነው። ቅስቀሳ አንዱ ክፍል ሊሆን ይችላል። ያሉትን የተለያዩ የትግል አማራጮች፤ እንዴት? በምን መንገድ? መታገል እንዳለባችሁ፡ ልትወስድ የሚገባችሁን ጥንቃቄ የመሳሰሉ ቁምነገሮችን የማስተማር ስራ ነው። ተቃዋሚው ውስጥ መወከል አለባችሁ። እቅድ ማውጣትን እቅዱን ለሁላችሁም ማድረስን ይፈልጋል። አጋዥ ስራዎችን መስራትና አመቺ ሁኔታዎችን ማመቻቸትም የተቃዋሚው ትኩረት መሆን አለበት።

ይህ መንገድ በመንግስቱ ጊዜ ውጤታማ የማይሆንበት ብዙ ምክንያት ነበር። በጊዜው እነዚህ ኅጠኞች

አገር የማፈራረስ ትግል ላይ ስለነበሩ መሳርያ የያዘውም ሆነ የበዛው ዜጋ የአገር ሉአላዊነት ከመንግስቱ አንባገነንት ቅድሚያ የሚሰጠው ነው የሚል አመለካከት ነበር። አሁን ግን ማድረግ የሚገባውን በአግባቡ ያወቀ ሰራዊት በታቀደው መሰረት ግዳጁን በመወጣት የመለስን መንግስት ፍጻሜ ለመስራት የማይችልበት ምንም ምክንያት የለውም። ይህ ስራ በመለስተኛ ደረጃ እንኳ ተሰርቶ ወይ አማራጭ ሆኖ ሁሉ እንዲያውቀው ተደርጎ ቢሆን በ1997 የትግሉ ምእራፍ በተዘጋ ነበር።

አሁንም ቢሆን ሁለተኛው አማራጭ ብቻ እራሱን ችሎ ውጤታማ ነው ለማለት አይደለም። እነዚህ ሁለት መንገዶች ተደጋጋፊነት እንዳላቸው እናውቃለን። ሁለት አማራጭ መንገድ እናዳለ በማሳየት ወደ አንደኛው መንገድ መሳብ እንዳለ ግልጽ ለማድረግ ነው። ይህ መሳርያ ለያዘው ብቻ አይደለም። የባንክ ሰራተኛውን ወይ ተማሪውን በሙሉ በድርጅታዊ አሰራር እንይዘዋለን ወይስ እንደስብስቡ በጋራ ድርሻው ምን እንደሆነ እንዴት የድርሻውን መወጣት እንዳለበት እናዘጋጀዋለን። ሁለ ገብ ህዝባዊ ትግል የምናደርገ ከሆነ ለትግል የማዘጋጀት ስራን ይፈልጋል። ሁሉንም መድረስና መያዝ አይቻልም። በጋር እንዲዘጋጅ ደግሞ መጀመርያ ሁሉም እንዳለበት ሁኔታ የድርሻውን በዝርዝር ማወቅ አለበት።

መሳርያ የያዛችሁት ከተቃዋሚው ጋር የተቀናጀ ትግል ሲታደርጉ የየትኛውም አይነት የዚህ አይነት እርምጃ በበዛ መልኩ በተቃዋሚው ብቃት የሚወሰን መሆኑ እውነት ነው። ይህ ማለት መሳርያ የያዛችሁት ትግሉ ላይ ያላችሁ ሀላፊነት ቀላል ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም። አንዴ ጊዜ ተወስኖ በምርምርና በጥናት ተደግፎ የተሰራው እቅድ ከውጣ በኋላ የድርሻችሁን በጥንቃቄና በሀላፊነት መፈጸም መቻላችሁን እርግጠኛ መሆን አለባችሁ። ለዚህ ደግሞ ተቃዋሚው ላይ አመኔታ ሊኖራችሁ ይገባል። እዚህ ላይ አመኔታ ተቃዋሚው ላይ የሚለው አላስፈላጊም ይሆናል ። ከተቃዋሚ በላይ በእቅዱ ላይ በሚነፍሰው የለውጥ ንፋስ ላይ አመኔታ ሊኖራችሁ ይገባል የሚለው የተሻለ ትርጉም የሚሰጥ ነው። አመኔታን የሚያሳጣ  የማይሆነው ቅድመ ህዝባዊ እንቢተኝነት ይኖራል። የቀረው የናንተ ድርሻ ነው ብሎ በሚናገር አይነት የለውጥ ንፋስ ቀድሞ በመላው ኢትዮጵያ ይነፍሳል። ያኔ በአንድ የቆመ የተባበረ ተቃዋሚ ይኖራል።

ሌላው መሳርያ የያዛችሁት ልትጠነቀቁበት የሚገቡ ጉዳዮች አሉ። የመጀመርያው ወያኔዎች አስመስለው (ፎርጅድ) እንቅስቃሴ ለመስራት መሞከራቸው አይቀርም። መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በጣም ከአልፈዘዛችሁ እስካሁን እንደታየው ይህን ያህል ውስብስብ አይደሉም። እንዲሸውድ አድርገው ሊሰሩት አይችሉም።

የፖለቲካ ፣የአይዶሎጂ የፖሊሲ ጉዳዮችን ለሌሎች ተዉት። አገራችን በአለችበት ሁኔታ ለቅንጦተኞች ከአልሆነ ለማንም ሁለተኛው የትግል መእራፍ ላይ መምጣት ያለበት ነው። ለነዚህ ጉዳዮች የተሻለም በቂ ጊዜ ወደፊት ይኖራል። ከፈለጉ ግን ሌሎች ይጨነቁበት። ትኩረታችሁ አንድና አንድ ለመልካም መለስና ግብራበሮቹን ማስወገድ አገር ማረጋጋት ህግና ስረአትን መልሶ ማምጣት ላይ ብቻ ይሁን። በይበልጥም የዘር ወይ የጎሳ ወጥመድ ውስጥ አትግቡ። በምንም ሁኔታ እራሳችሁን እዚህ ውስጥ ከአገኛችሁት ትከፋፈላላችሁ ይህ ከሆነ ደግሞ አላስፈላጊ መሰዋትነት ይኖረዋል። መሳርያ የያዘው የተሳተፈበት እንቅስቃሴ ከተደረገ በኋላ  የመሆን እድሉ የጠበበ ቢሆንም ምን አልባትም መለስና ስብስቦቹ ተርፈው ይወጣሉ። ይህ ከሆነ ሊያስከትልባችሁ የሚችለው አደጋ ቀላል አይሆንም።

በእቅዱ መሰረት ስራዎች መከናወናቸውን እርግጠኛ ሁኑ። ጊዜው ሲደርስ ይህን የበሰበሰ መንግስት እድሜ ለማርዘም የሚደረግ ምንም አይነት አስተዋጾ ከዚህ ቀን ጀምሮ ወንጀል ይሆናል የሚል በአዋጅም መልክ ይሁን በስምምነት እቅዱ ውስጥ ይኖራል። አለመታዘዝ ወይ አላስፈላጊ መገዳደር የሚያደርጉ ላይ ለናንተም ስራውን የሚሰሩ ሌሎች ዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ነጻ እርምጃን መውሰድ ስምምነት ላይ ሊደረሰብት ይገባል። በአዋጁም መልክ ይሁን በስምምነት ይህ እርምጃ በምን አይነት አስገዳጅ ሁኔታዎች ሰኖሩ ቢፈጸም ህጋዊ እንደሚሆን በዝርዝር የሚያስቀምጥ መሆንም አለበት። የዚህ አይነት እርምጃ ስህተት ከተሰራ ማረም አይቻላም። በጣም ጥንቃቄን ይፈልጋል። በታቀደው መሰረት ያለ ምንም ሴማታዊነት መፈጸሙን እርግጠኛ መሆኑ ላይ  ጥንቃቄ መውሰድ ያስፈለጋል።

መሳርያ የያዘውንም ሆነ ጠበቃውን ወይ የባንክ ሰራተኛውን በግልጽ ለማይቀረው ትግል ዝግጁ ለማድረግ ሲሞከር ሚስጥር ከመጠበቅ አስፈላጊነት ጋር ማቻችል ያስፈልጋል። ይህም ሌሎችም ጽሁፎቻችን የተለመደውን የሚስጥር መስመር እንደሚተላለፉ እናውቃለን። ተቃውሞም እየደረሰን ነው። ሚስጥራዊነት ብለን ያበጀነው ማሰርያ ከዚህም በላይ ሳይታለፍ እንዴት ህዝባዊ ትግል እንደሚደረግ የትኛውንም ክፍል ለትግል ማዘጋጀት እንደሚቻል ግልጽ አልሆነልንም። ሁሉም ዜጋ ተመሳሳይ አስተዋጾ ትግሉ ላይ ማድረግ አይችልም። እንዳለንበት ሁኔታ ልናደርገው የምንችለው አስተዋጾ የተለያየ ነው። ሆ ብለን እንነሳ የሚለው የተደጋገመ ጥሪ ውጤታማ ያልሆነበት አንዱ ምክንያት ሆብለን ተነስተን ምን እናድርግ? የሚለው ለማኝኛችንም ምንም ስላልገባን ነው። ሁሉም ትርጉም በሚሰጥ መንገድ ድርሻውን ማወቅ አለበት። እኛ ተቃዋሚዎች ብለን ጀምረን፣ በወያኔ ስር ቢሆኑም የህዝብ ተውካዮች ብለናል፣ አሁን ደግሞ መሳርያ ስለያዘው ድርሻ እናወራለን። ነገ ደግሞ የእምነት ድርጅቶች ወይ በውጪ ያለው ኢትዮጵያዊ እያልን እንቀጥላለን።

ተቃዋሚዎች በመጨረሻ ተሳክቶ ለታላቅ አገራዊ ጉዳይ ጉባኤ የሚቀመጡ ይመስላል። ይህን ትግል በቶሎ በአሸናአፊነት ለመቋጨት በጣም አስፈላጊ እርምጃ ነው። እኛም የበዛውም ዜጋ ጉትጎታችን ተሰማ። መተባበሩ ትግሉን በአሸናፊነት ለማጠናቀቅ የግድ መሆን ያለበት ነው እንላለን።

የዚህ ጉባኤ አስፈላጊነትና አስቸኳይነት ጉበአተኞቹን አንድ አይነት ስምምነት ላይ እንዲደርሱ እንደሚያደርጋቸው ምንም ጥርጥር የለንም። እኛን የሚያሳስበን ይህ አጋጣሚ ከተፈጠረ በአንድ ተሰብስቦ መነጋገር ከተቻለ; አሸናፊ የሚያደርገንን ታላቅ የትግል እቅድ ምሁራኖቻችን አርቅቀው ማቅረብ ታስቧቸዋል ወይ?። ወይ በየመወያያ ክፍሎች 24/7 ፖለቲካውን በተለያየ ጎኑ ስናደቅ የምንውለው ይህ ሁሉ ጨንቅላት ተጨምቆ አሸናፊ የሚያደርገንን እቅድ በወረቀት ማስቀመጥ ይቻለናል?። የጉባኤው ታዳሚዎች የተለያየ አማራጭ ቀርቦላቸው አዋህደውትም ቢሆን ስምምነት ላይ ደርሰውበት አጽድቀውት የወጣሉ?።

ትብብሩ እቅዱን ለመተግበር ወይ በዚህ ጽሁፍ ያነሳናቸውን አይነት ቁም ነገሮችን ተግባራዊ ለማድረግ ብቃት ይኖረዋል? የሚለውም አሳሳቢ ነው። ትብብሩ ብቻ በራሱ አሸናፊ እንደማያደርገን ለማንም የተሰወረ አይደለም። ያም ሆነ ይህ የህዝብን አመኔታ መስራት የቻለ ተቃዋሚ መሳርያ የያዘውንም አመኔታ በቀላሉ ያገኛል። የድርሻችንን ሳንሰራ መሳርያ የያዘውን የመለስ ነህ ስላልነው የመለስ ንብረት አይሆንም ትግሉንም ትርጉም በሚሰጥ መንገድ አያግዝም።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተለመደ እንግዳ ነገር መሆን ከጀመረ ቆይቷል ይህ በአገራችን አቆጣጠር ከታህሳስ ሶስተ 2004 ዓ/ም አንድ ወር ቀደሞ ነው የሆነው። እለቱ የስራ ቀን ነው። ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰአት ከሀምሳ ዘጠኝ። እስከ ሁለት ከሀምሳ ዘጠኝ በአለው ሰአት ነው የሆነው።

ለሁሌው በዚህ ሰዓት የትራችክ መጨናነቅ የተለመደ ነው። ይህንን ለየት ያደረገው ከጠዋቱ አንድ ሰአት ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ መንገዱን ሞልተው የቆሙት መኪናዎች ሁሉ ሹፌር አልነበራቸውም። ሁሉም ሞተራቸውን አጥፈተው ነበር የቆሙት።

ከየትራንስፖርቱ መኪና የወረደው ተሳፋሪ መኪናውን ቆልፎ ከወጣው ሹፌር ጋር ተዳምሮ የእግረኛ መተላለፊያው መንገድ በሰው ብዛት ተጨናንቋል። የእለት ገበያቸውን በጠዋት ሊስትሮዎችና በየመንገድ ዳር ያሉ ቁርስ ቤቶች ዘግተዋል።

ቤተመንግስት ውስጥ ጫጫታ በርክቷል። ለአንድ ሰአት ብቻ የሚቆይ ሰላማዊ ተቃውሞ መሆኑን ከሰሙም በኋላ ሊረጋጉ አልቻሉም።

ጸጥታ አስከባሪዎችና የትራፍክ ፖሊሶች ትራፊኩ የተለመደ እንቅስቃሴውን እንዲጀምር እንዲያስገድዱ በጨቀጨቁም ፍላጎቱ አልነበራቸውም። ብዙዎቹ በየመንገድ ዳር ከተሰበሰበው ህዝብ ጋር የደራ ጨዋታ ይዘዋል። ይህ መንግስት ያበቃለት ነው። እንዳቦካው ይወጣው ሲሉ የተሰሙም አሉ።

ህዝባዊ ተቃውሞው ለአንድ ሙሉ ሰዓት የቆየ ሲሆን በእለቱ ተማሪዎችም ሰራተኞቹም አንድ ሰአት

**ዘግየተው ነው የቀን መርሀ ግብራቸውን የጀመሩት።**

**ዳኮታ የጥናት መአከል**

dakotareserch@yahoo.com